# የተደናቀፈው ትግላችንና፣ የድል አጥቢያ አርበኞች

ምርጫ 97 አስከትሎ ተቀጣጥሎ የነበረው ትግላችን ለምን እንደ ጤዛ ጠኋት ታይቶ በረፋዱ እንደጠፋ በእኔ እይታ ምክንያት ያልኳቸውን አንዳንድ ሁኔታዎች በአጭሩም ቢሆን ለመዳሰስ እሞክራለሁ። ይህ እንደ ክረምት ጸሀይ ብልጭ ብሎ ድርግም ያለው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብን ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ አነሳስቶና አስተባብሮ ነበር ተብሎ የተነገረለት ጸረ የወያኔ አገዛዝ ትግል በወቅቱ እውነትም ሕዝቡ በአረመኔውና ጠባብ ብሄርተኛ በሆነው የወያኔ አገዛዝ ለ14 ዓመታት ሲረገጥ ከቆየ በኋላ ከዛሬ ነገ ይሻለዋል እየተባለ ነገር ግን ከቀን ወደቀን ግድያው፣ አፈናው፣ እስራቱና ጭቆናው አላባራ በማለቱና ሕዝብም ሊሸከመው ከማይችልበት ደረጃ በመድረሱ፣ አገዛዙም ባለው አኳኋንም ሊቀጥል ከማይችልበት ሁኔታ ላይ ስለነበረ ለዚህ በአናቱ ላይ ተንዘራፍጦ ገደብ ባጣ ሁኔታ ሕዝብን ለሚመዘብረውና ለሚያጎሳቁለው ጠባብ ብሄረተኛ የሆነ አምባ ገነን አገዛዝ ባሳደረበት ጥላቻ የተነሳ ለጊዜውም ቢሆን ይህንን የንዑስ ብሄር አምባገነን አገዛዝን ለመቃወም ብሎም ከስልጣን ለማውረድ ባለው ጽኑ ፍላጎት የተነሳ ባማናቸውም ጸረ ወያኔ በሆነ ስብስብ ስር በመደረጀት ድምጹን ለጸረ ወያኔ ለሆኑ ድርጅቶች በመስጠት በምርጫ 97 ለአለው አገዛዝ ያለውን ጥላቻና ለመሰረታዊ ለውጥ ያለውን ጻኑ ፍላጎት ካርዱን በመጠቀም ለተቃዋሚ ድርጅቶች ድምጹን በመለገስ ይህንን ሰው በላ አገዛዝ ለጊዜውም ቢሆን ተፈጥራ በነበረችው የተስፋ ጭላንጭል በመጠቀም ፍላጎቱንና ምኞቱን ለአንዴም ለመጨረሻም በተሰጠው እድል ተጠቅሞ በማያሻማና በማያዳግም ሁኔታ አስረግጧል።

ይህንንም ሕዝባዊ ውሳኔ ለመቀበል አምባገነኑ ወያኔ ተፈጥሮው ስለማይፈቅድለት ጸረ ሕዝብ መሆኑን፣ የጭካኔ በትሩን በማንሳት ደም የተጠሙ የአጋዚ ሰራዊቱንና የጸጥታ ክፍሎቹን በሕዝብ ላይ በማሰማራት፣ ኮሮጆ በመገልበጥና በመስረቅ አይኑን በጨው ታጥቦ አሸናፊ እኔ ነኝ በማለት የድል አድራጊውን የፓርቲ አባላትና ደጋፊዎቻቸውን አለርህራሄ በመግደል፣ በማሰር፣ በማሳደድና በማዋከብ የድሉ ባለቤት የሆነውን ሰፊውን ሕዝብ እጁ ሊያስገባ የነበረውን የሕዝብ ንብረት የሆነውን በትረ ስልጣን እጁ እንዳያስገባ አድርጓል። ወትሮውንም የምርጫ 97 የተቀናቃኝ ፓርቲዎች እንዲሳተፉ የተደረገው አምባ ገነኑ አገዛዝ ፍርፋሪ ለሚጥሉለት የምዕራባውያን መንግስታት ባደረጉበት ጫና የተነሳ ሕዝባዊና ዲሞክራሲያዊ መስሎ ለመታየት ያሳየው የይስሙላ ድራማ እንደነበር የወያኔን ማንነትና ምንንነት አስቀድመው በደንብ ለተረዱትና ለሚያውቁት፣ በምርጫ ሊሸነፍ እንደሚችል ቢያምኑም ነገር ግን በምንም አይነት ተአምር ቢሆን ወያኔ በእጁ ያለውን ስልጣን ለሌላ በምርጫ ተሸንፌአለሁ ብሎ ስልጣኑን አሳልፎ እንደማይሰጥ በወሰደው የወንበዴ እርምጃ እምብዛም  አላስደነቃቸውም።

በመሰረቱ ለምርጫ 97 ብሎም ከምርጫው ባሻገር ላለውና ሊመጣ ለሚችለው ክስተት የተቃዋሚ ድርጅቶች ሕዝቡን ሲያሰባስቡና ሲያደራጁ ለሚደግፏቸው ሕብረተሰብ ንቃተ ህሊናውን ለማዳበርና ለረጅሙና ለመራራው ትግል በቁርጠኝነት ታጥቆ እንዲነሳና እንዲጠብቅ ምን ያክል አዘጋጅተውት ነበር? የወያኔ አገዛዝ ጸረ ሕዝብ፣ ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ አንድነት እንደሆነ፣ የሕዝብና የሐገር ዋነኛ ጠላት

መሁኑን፣ ስለሆነም ያለአንዳች አማራጭ መወገድ እንዳለበት ባገርና በሕዝብ ያደረሰውን ስፍር ቁጥር የለሽ በደልና ማፈራረስ ምን ያክል እንዲገነዘብ አድርገውታል? በስልጣን ላይ ያለው አገዛዝም ስዩመ እግዚአብሄር እንዳልሆነና በሕዝብ ያልተመረጠ፣ ስለሆነ ሕዝብን እንደማይወክል፣ ሕዝብ እራሱ የራሱን መሪ መምረጥ መቻል ብቻ ሳይሆን የመረጠውንም መሪ ካልተስማማው ለስልጣን እንዳበቃቸው ሁሉ ከስልጣንም አውርዶ በሌላ ባመነበት የሕዝብ ወገን አመራሩን ሊተካ እንደሚችል ምን ያክል ተገንዝቦታል? አስተምረውታልስ? እንዚህንና የመሳሰሉትን ህበረተሰቡ እንዲረዳ ጥረት ተደርጎ ነበር? ሕብረተሰቡስ እነዚህ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ለወደፊት አገሪቷን እንዴት አድርገው እንደሚያስተዳድሩና ወዴት ሊመሩት እንደሚችሉ የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን ለሕዝብ እንዲዳረስ በማድረግ ሕብረተሰቡ የሁሉንም የተቀናቃኝ የፖለቲካ ቡድኖች አላማና ግብ ተወያይቶበት ከዚህኛ ይሄኛው፣ ወይንም፣ ያኛው፣ በማለት በተቀናቃኝ ድርጅቶች መካከል አመዛዝኖ የሚበጀውን የፖለቲካ ቡድን መምረጥ እንዲችል ምን ያክል ተሰርቶበታል? በትግል ውስጥ ሊኖር የሚችለው ውጣ ውረድ እረሃብ፣ እስራት፣ግርፋት ብሎም በህይወት መሰዋትን እስከመክፈል ሊያመጣበት እንደሚችል ተረድቶት ነበርን? ወደትግሉ ዓለም ሲቀላቀልስ በውዴታ እንጂ በይሉኝታና በአንዳንድ ግፊቶች እንዳልሆነ አውቆና አምኖ እንዲሆን የተደረገው ጥረት እስከምን ድረስ ነው? ትግሉም እረጅምና መራራ ሊሆን እንድሚችል፣ የሚያራምዱት ትግል ምንም እንኳ ሰላማዊ ትግል ቢሆንም ቅሉ በአንፃሩ ግን መሳሪያ አንስተው ከሚታገሉ ክፍሎች የሚጠይቀው የህይወት መስዋትነት በጣም ያነስ ቢሆንም ነገር ግን ቀላል ያልሆነ መስዋዕትነትን ሊያስከፍል እንደሚችል ምን ያክል ግንዝቤ እንዲኖራቸው ተደርጓል? እነኚህንና የመሳሰሉትን የፖለቲካ አካሄድና ገጠመኞች ሊኖሩ እንደሚችሉ ጠለቅ ባለ መልኩ ግንዛቤ ኖሮት ትግሉን እንዲቀላቀል ንቃተ ህሊናውን በሚገባ አዳብሮ ከሞላ ጎደል በአስተማማኝ ሁኔታ በሕብረተሰቡ ስነልቡና ሰርፆ ሲገባ ብቻ ነው ትግሉ ፍሬያማና ውጤታማ ሊሆን የሚችለው።

ይህንንና የመሳሰሉት መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት ሁኔታ የትግሉ አደረጃጀትና የሕብረተሰቡ ንቃተ ህሊና ባልዳበረበት ጎራ፣ ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት የሚደረገው ትግል የተጠበቀበትን ፍሬ አፍርቶ ለድል ሊያበቃ አይችልም። ይኸም የተሟላበት መድረክ ባለመኖሩ ዛሬ ከደረስንበት አሳዛኝ ሁኔታ ለመድረስ ከመብቃታችን ባሻገር ምስጥ እንደበላው እንጨት ተቦርቡሮ ሊወድቅ የደረሰውን ይህንን የጠባብ ብሄርተኛ አገዛዝ መጣል ተስኖን አሁን ከምርጫ 97 በፊትና ከዚያም ባሻገር ለተወሰኑ ወራትም ቢሆን በተቃዋሚው ጎራ የነበረው አንድነትና ሕብረት ተሸመድምዶ ከምን ጊዜውም በላይ በተዳከመ ሁኔታ ላይ ይገኛል። ይህም ክስተት ባደራጁት ሕብረተሰብ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የፖለቲካ ፓርቲዎችንም በበላይነት ይመሩና ሕብረተሰቡን ያደራጁ በነበሩት ቱባ ቱባ የፖለቲካው የበላይ መሪዎች ሳይቀር ጎልቶ መታየት ጀምሯል። ዛሬ እንኳን ተከታያቸውን ማሳመን ቀርቶ በመሃከላቸው ቀዳሚ ጠላት የሆነው የትግሬ ወያኔ ነው በሚለው ሃሳብና ሌሎችም አመለካከቶች ላይ ጭምር መስማማት ባለመቻላቸው እርስ በእርሳቸው ከሶስትና ከአራት ቦታ ተከፋፍለው ደጋፊዎቻቸውም በዚያው አኳያ ሶስትና አራት ቦታ ተሰነጣጥቀው የሐገርና የሕዝብ ጠላት የሆነውን የአምባ ገነኑን መንግስት ታግሎ ከመጣል ይልቅ ተቃዋሚ ተብዬዎቹ እራሳቸው አንዱ አንዱን ለመጣል የሚጠፉት የሰው ኃይልና ጊዜ በዕውን ጠላት ማን እንደሆነ ለመለየት እስከሚያዳግትበት ደረጃ ሰለተደረሰ የጎጠኛው መንግስት የቆሰለ ጥንቸል እንዳልነበረ ሁሉ በተቃዋሚዎች የፖለቲካ አቋምና ጥራት ጉድለት የተነሳ ጸረ ሕዝብ የሆነው ወያኔ እራሱን እንደገና እንዲያገግምና እንዲደራጅ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ከማበርከቱም በላይ ለወደፊትም ለሚደረገው ሕዝባዊ አመጽና ትግል

ካለፈው በከፋ ሁኔታ አዳጋችና አስቸጋሪ እንዲሆን የተመቻቸ ሁኔታዎችን ለወያኔ በመፍጠር አሌ የማይባል አስተዋጽዖ እየተደረገ ለመሆኑ ለማንም በረጋ አይምሮ ማሰብ ለሚችል የተሰወረ አይደለም። እንደ እውነቱ ከሆነ ሕዝብ በኀጠኛው የወያኔ አገዛዝ ላይ ባለው ከፍተኛ ጥላቻ የተነሳ ማንም ይሁን ምንም ወያኔን ከስልጣን የሚያስወግድለትን በመሻቱ የተነሳ የተቃዋሚ ድርጅቶችን ለመምረጥ ተገደደ እንጂ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሰረታዊ የሆነ የፖለቲካ ንቃተ ህሊና ሕብረተሰቡ እንዲያገኝ፣ ጠላቱንና ወዳጁን ለይቶ እንዲያውቅ፣ የሚቃወመውም በምንና እንዴት እንደሆነ፣ ትግሉም ሊወስድ የሚችለው ጊዜና ሊያስከፍል የሚችለው መስዋዕትነት ምን ያክል የከፋ ሊሆን እንደሚችል በሚገባ ስላስተማሩት አልነበረም። ስለሆነም የሕብረተሰቡም ሆነ የአደራጆቹ የንቃተ ህሊና ውሱን በመሆኑ ምክንያት ያለውን የአምባ ገነን አገዛዝ በተመጣጠነ መልኩ ለመመከት ብሎም ለድል ለመድረስ የሚያስችል የበሰለና የተቀነባበረ ስላልነበረ አመራሩም ለሶስትና አራት ቦታ ሲከፋፈል ሕብረተሰቡም በዚያው መጠን በቀላሉ ለመበታተን በቅቷል።

ከላይ የተዘረዘው ክስተት በሐገር ቤት ባለው ህብረተሰብ ላይ የሚታይ ብቻ አልነበረም፣ ይህ ሁኔታም በምዕራቡ ዓለም በሚገኘውም ኢትዮጵያዊ ጭምር በተመሳሳይ ወይንም በከፋ ሁኔታ ሲንጸባረቅ ይታያል። ይህ በምዕራቡ ዓለም የሚገኘው የተቃዋሚ ደጋፊ የሆነው ክፍል በአብዛኛው የድል አጥቢያ አርበኛ ከመሆኑም በላይ ልክ እንደ ሐገር ቤቱ ሕብረተሰብ ያልተደራጀና በተገኘችው አጋጣሚ ግማሹ በቅንነት ትግሉን ለማገዝ ሲቀላቀል የተቀረው በተለይ እራሱን ምሁር ነኝ ብሎ የሚገምተው ክፍል የራሱን ለወደፊት ሊኖረው የሚችለውን የስልጣን እርከን ከማለም እንደነበር ከምርጫው በኋላ ያሳዩት የነበረው የተለመደ የድል አጥቢያ አርበኞች ድራማ ለመረዳት ይቻላል። ይህ ቡድን የትግሉን መድረክ ከንጹህን ታጋዮች እጅ በመንጠቅ ባልሰሩበትና ባለፉበት ግንባር ቀደም ተዋንያን በመሆን እነሱ ተናጋሪ፣ እነሱ አማካሪ፣ እነሱ ተቺ፣ እነሱ ጸሐፊና ከኛ በላይ ማን አውቆ ባዮች እንደነበሩ በቀላሉ ልንዘነጋው የማይገባን የትላንትናው ትዝታችን ነው።

በምርጫ 97 የወያኔ ሽንፈት እውን እንደሆነ ይሄው አድር ባይ የሕብረተሰብ ክፍል ካለው ራስ ወዳድነት በመነጨ ስንካላ እምነት የተነሳ የድሉ ባለቤት የሆኑትን የተቃዋሚ ፓርቲው አባላት ዘንድ ወደ ሐገር ቤት ቀን በቀን በመደወል፣ በመፃፍ፣ እኔ ዶ/ር እከሌ ነኝ፣ እኔ ፕሮፌሰር እከሌ ነኝ፣ እኔ ደግሞ ኢንጂነር እከሌ ነኝ ወዘተ... በማለት አብረን ሁለተኛ ደረጃ ከነከሌ ነበርን እኮ፣ ከነ እከሌ ጋር ደግሞ ኮሌጅ ውስጥ አብረን ነበርን፣ ያቶ እከሌ ልጅ ነኝ፣ የወይዘሮ እከሊት ወንድም ነኝ ወዘተ... አታስታውሰኝም እንዴ? በማለት በሽንገላ፣ የሰራችሁት ስራ መቼም ግሩምና የሚያስመሰግናችሁ ነው፣ እኔም እኮ ለናንተ እዚህ ባለሁበት ይሄን፣ ይሄን፣ እየሰራሁ ነው በማለት የአስታውሱኝ ውትወታ ብቻ ሳይሆን ቤትና ንብረቱንም ሸጦ ሻንጣውን አንጠልጥሎ ባለፋበትና ባልታገለበት የሕዝብ ትግል ወደ ሐገር ቤት ተንደርድሮ ለመግባት በዘመድ፣ በጓደኛ፣ በአበልጅነትና አብሮ አደግነት ምክንያት ተጠማጥሞ ሐገሩ ገብቶ ስልጣን ለመቀላወጥ አኮብኩቦ የነበረው ቁጥር ስፍር እንዳልነበረው ከማንኛችንም የተሰወረ አልነበረም። ይህንንም ጉዳይ እራሳቸው የተቃዋሚው ተመራጭ የነበሩት የሚመሰክሩት ያደባባይ ሚስጢር ነው። ታዲያ ይኸው አድር ባይ የድል አጥቢያ አርበኛ ምሁር ነበር ስለ ሐገራችን የፖለቲካ አካሄድና ምን መደረግ እንዳለበት በየ እሬዲዮው፣ መጽሄቶችና ድህረገፆች ሲያታክተን የነበረው፣ ታዲያ እነኚህ በሆዳቸው የሚያስቡ ምሁሮቻችን ዛሬ የት ጠፉ ብለን ለመጠየቅ የተገደድነው? ትግሉ ግቡን ስለመታ ይሆን? ወይንስ ያሰቡት ስላልተሳካ አሁንም ስልጥኑን የያዘው ይሄው የጠባብ ብሄርተኛው የወያኔ አገዛዝ

ስለሆነ ወያኔ ጥርሱን እንዳይነክስባቸው በየጉድጓዳቸው ተደብቀው ይሆን? አሁን ያለውም ይሁን ሌላ የፖለቲካ ድርጅት በድንገት ቢያንሰራራና ለወያኔው አገዛዝ እንዳለፈው ምርጫ 97 ለስልጣኑ በሚያሰጋው ሁናቴ ቢገጥመው አሁንም አስራ አንደኛው ሰዓት ላይ ብቅ ብቅ ማለት ይጀምሩ ይሆን? የሚቀር ትዕይንት አይመስለኝም! ያድር ባይ ጸባይ በቀላሉ ሊተነብይ ስለሚችል ይህንን ቀድሞ ለመናገር ነብይነትን አይጠይቅም። መልሱን ለራሱ በሆዱ ለሚያስበው መተዉ ይበጃል። አድር ባዮችና የድል አጥቢያ አርበኞች ከእውነተኛ ታጋዮች ላይ ትግሉን ችቦ በመቀማትና በመጨረሻው ሰዓት ብቅ ብቅ በማለት፣ መድረኩን ለመቆጣጠር፣ ቀዳሚ ተዋንያን መሆን፣ ከኛ በላይ ላሳር ማለት፣ የተለመደና ለወደፊትም የሚኖር ስለሆነ በድል አጥቢያ አርበኞች ላይ እምብዛም ጊዜዬን ሳላጠፋ ይህንን ያክል ስለነሱ የተፈጥሮ ባህሪይ ከተቸሁ ይበቃኛል።

በመጨረሻም አሁን ያለውን አገዛዝ ለመጣልና ሕዝብን የስልጣን ባለቤት ለማድረግ በቅድሚያ አገዛዙ ጸረ ሕዝብና ጸረ ኢትዮጵያ ነው በሚለው ሀሳብ ላይ ሁሉም አንድ የሆነ አቋም ከሌላቸው ሕብረተሰቡንም ትግሉ መራራና እረጅም ከመሆኑም ባሻገር የህይወት መስዋዕነትን እንደሚጠይቅና ለሚታገለውም ሕዝባዊ ዓላማ የጠራና የዳበረ ግንዛቤ እንዲያገኝ መሰረታዊ የሆኑ የፖለቲካ ግንዛቤን በማስጨበጥ ንቃተ ህሊናውን ከምን ጊዜውም በላይ እንዲያዳብር ከፍተኛ የሆነ ትምህርታዊ ዘመቻ መካሄድ ይኖርበታል፣ ይህ በሐገር ቤት ላለው ሕበረተሰብ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በውጪውም ዓለም ላለው የትግል አጋሮች ሁሉ ተግባራዊ ሆኖ መስራት ካልተጀመረ ያልነቃና ያልተደራጀ ትግል ትላንት ምን እንዳደረሰ ያየነውና ትምህርትም ያገኘንበት ስለሆነ ካለፈው ስህተታችን ተምረን የወደፊቱን የትግል ዘዴ በመንደፍ ለድል የሚያበቃን በደንብ የተዋቀረ፣ የነቃና የተደራጀ የሕብረተሰብ ክፍል የመፍጠሪያው ጊዜው አሁን ነው።

አሰግድ መታፈሪያ

ቸር ይግጠመን

ድል ለየኢትዮጵያ ሕዝብ